# የተጨማሪ እሴት ታክስ ምዝገባ ሲሰረዝ በእጅ ያለ እቃን ዋጋ ስለማስላትና የተከፈለ ታክስ ስለሚቀናነስበት ሁኔታ የወጣ መመሪያ

የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን

ነሐሴ 2001 ዓ.ም.

አዲስ አበባ

## *የተጨማሪ እሴት ታክስ ምዝገባ ሲሰረዝ በእጅ ያለ እቃን ዋጋ ስለማስላትና የተከፈለ ታክስ ስለሚቀናነስበት ሁኔታ*

## *የወጣ መመሪያ ቁጥር 24/2001*

የተጨማሪ እሴት ታክስ ከፋዩ የምዝገባ ሰርተፊኬት እንዲሰረዝ ጥያቄ በሚያቀርብበት ጊዜ የካፒታል እቃዎችን ጨምሮ ሌሎች በእጅ በሚገኙ እቃዎች ላይ የተከፈለን ተጨማሪ እሴት ታክስ በማሰብና በማቀናነስ ረገድ ያለውን አሠራር በግልጽ ማስቀመጥ አስፈላጊ ስለሆነና ለዚሁ የሚረዳ መመሪያ መውጣት እንዳለበት በአዋጁ ላይ የተመለከተ በመሆኑ፣

የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን በተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ቁጥር 285/1994 አንቀጽ 4(8) እና በሚኒስትሮች ምክር ቤት የተጨማሪ እሴት ታክስ ደንብ ቁጥር 79/1995 አንቀጽ 39 በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ይህን የአፈፃፀም መመሪያ አውጥቷል፡፡

### 1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "የተጨማሪ እሴት ታክስ ምዝገባ ሲሰረዝ በእጅ ያለ እቃን ዋጋ ስለማስላትና የተከፈለ ታክስ ስለሚቀናነስበት ሁኔታ የወጣ መመሪያ ቁጥር 24/2001" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### 2. ትርጓሜ

ለዚህ መመሪያ አፈፃፀም፡-

1) "የካፒታል እቃ" ማለት ለተጨማሪ እሴት ታክስ ተመዝግቦ ታክስ ለሚከፈልበት የንግድ ሥራ እንዲያገለግል ግዢ የተፈፀመበትና የንግድ ሥራውን ለማስፋፋት የዋለ ቋሚ እቃ ማለት ነው፡፡
2) "የተጨማሪ እሴት ታክስ ምዝገባ ስረዛ ጥያቄ" ማለት በተለያዩ ምክንያቶች ታክስ የሚከፈልበትን የንግድ ሥራ ለማቆም ወይም ከተጨማሪ እሴት ታክስ ከፋይነት ለመሰረዝ የሚቀርብ ጥያቄ ነው፡፡

E

3) “የታክስ ማቀናነስ” ማለት ታክስ የሚከፈልበትን ተግባር ለማስቀጠል በዋለው ቋሚ እቃ /ካፒታል/ ወይም ሌሎች በእጅ በሚገኙ እቃዎች ላይ የተከፈለ ተጨማሪ እሴት ታክስን ክሬዲት ማድረግ ነው፡፡

4) “የንብረት የአገልግሎት ዘመን” ማለት የካፒታል እቃው ከተገዛበት ጊዜ ጀምሮ የምዝገባው ሥረዛ ጥያቄ እስከቀረበበት ቀን የሰጠው የአገልግሎት ጊዜ ነው፡፡

5) “የተመዘገበ ሰው” ማለት ለተጨማሪ እሴት ታክስ ተመዝግቦ የመለያ ሰርተፊኬት ይዞ የሚገኝ ድርጅት ወይም ግለሰብ ነው፡፡

6) “ታክስ” ማለት የተጨማሪ እሴት ታክስ ነው፡፡

## 3. በምዝገባ ስረዛ ጊዜ ስለሚፈፀም የታክስ ማቀናነስ

1) የተመዘገበ ሰው ታክስ የሚከፈልበትን ግብይት በማቆም የምዝገባ ሥረዛ ሲጠይቅ፣ በእጁ የሚገኙ ታክስ የሚከፈልባቸው አቅርቦቶች እና/ወይም የካፒታል እቃዎች ታክስ በሚከፈልበት የግብይት ዋጋ እንደተሸጡ ይቆጠራሉ፡፡

2) ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) አፈፃፀም በእጅ የሚገኙ እቃዎች ታክስ በሚከፈልበት የግብይት ዋጋ እንደተሸጡ ይቆጠራል ማለት ታክስ ከፋዩ ባልተሸጡት ዕቃዎች ላይ የሚመለስለትም ሆነ የሚከፍለው የተጨማሪ እሴት ታክስ የማይኖር መሆኑን የሚያመለክት ነው፡፡

3) በእጁ የሚገኙ ታክስ የሚከፈልባቸው እቃዎች ላይ የተጠየቀው ክሬዲት ወይንም ተመላሽ ሊቀናነስ የሚችለው የምዝገባ ስረዛ ጥያቄ ሲቀርብ በተከናወኑ ግዥዎች የእያንዳንዱን የግዥ ዋጋ መሠረት በማድረግ በሚሰላው ታክስ ይሆናል፡፡

## 4. በምዝገባ ስረዛ ጊዜ በእጅ በሚገኙ የካፒታል እቃዎች ላይ ስለሚታሰበው ታክስ

1) በምዝገባ ስረዛ ጊዜ በካፒታል እቃዎች ላይ የተያዘ ክሬዲት ሊቀናነስ የሚችለው እያንዳንዱ ቋሚ እቃ የተገዛበትን ዋጋና ጊዜ በተናጠል ለይቶ በማስላት ይሆናል፡፡

2) የካፒታል እቃዎች የአገልግሎት ዘመን

በገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 286/94 አንቀጽ 23 (5) መሠረት የካፒታል እቃዎች የአገልግሎት ዘመን፡-

ሀ. የኮምፒዩተርና የሶፍት ዌር ውጤት 4 ዓመት

ለ. ሌሎች ማናቸውም የንግድ ሥራ ቋሚ ንብረቶች 5 ዓመት

ሐ. የህንፃዎች 20 ዓመት ይሆናሉ፡፡

3) የካፒታል እቃ ቀሪ ዋጋ ስሌት

ሀ/ የካፒታል እቃ ቀሪ ዋጋ ላይ ለመድረስ የሚከተሉትን መሠረት በማድረግ ይሰላል፡-

$$\left(\frac{\text{ሀ}}{\text{ለ}} \times \text{ሐ}\right) = \text{መ}$$

<u>***መግለጫ***</u>

ሀ = የንብረቱ ቀሪ የአገልግሎት ዘመን

ለ = የንብረቱ ጠቅላላ አገልግሎት ዘመን

ሐ = የካፒታል እቃው ወጪ /ዋጋ /Acquisition cost/

መ = የካፒታል እቃው ቀሪ ዋጋ /Book value/

ለ/ የሚከፈል ወይም የሚቀናነስ ታክስ አሰላልን በተመለከተ ከላይ የተመለከተውን መግለጫ መሠረት በማድረግ እንደሚከተለው ይሆናል፡፡

$\text{ሠ} = \text{መ} \times 15\%$

<u>***መግለጫ***</u>

ሠ = የሚከፈል/የሚቀናነስ ታክስ

መ = የካፒታል ዕቃው ቀሪ ዋጋ

በዚህ ቀመር መሠረት ተሰርቶ የተገኘው ታክስ (ሠ) ከተጠየቀው ወይም ከተያዘው ክሬዲት እንዲቀናነስ ይደረጋል፡፡

## 5. የመመሪያው ተፈፃሚነት

ይህ መመሪያ በባለሥልጣኑ ዋና ዳይሬክተር ከተፈረመበት ቀን ጀምሮ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ ------------------------ ቀን 2001 ዓ.ም

መላኩ ፈንታ
የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን
ዋና ዳይሬክተር

E